የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 55.
ADDIS ABABA 11th August, 2008

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፯/፪ሺ ዓ.ም

ለከተሞች የአካባቢ አስተዳደር ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፩፻፺፮

**Proclamation No. 597/2008**

International Development Association Financing Agreement for the Urban Local Government Development Project Ratification Proclamation Page 4196

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፯/፪ሺ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለከተሞች የአካባቢ አስተዳደር ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፺፫ሚሊዮን ፰መቶሺ ኤስ.ዲ. አር /ዘጠና ሦስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፲፫ ቀን ፪ሺ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፬ ቀን ፪ሺ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለከተሞች የአካባቢ አስተዳደር ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፯/፪ሺ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 597/2008.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 93,800,000 SDR (ninety three million eight hundred thousand Special Drawing Rights) for financing Urban Local Government Development Project was signed in Addis Ababa on the 13th day of June, 2008;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the agreement at its session held on the 1st day of July, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Sub-Article (1) and (12) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for the Urban Local Government Development Project Ratification Proclamation No. 597/2008".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፲፫ ቀን ፪ሺ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 4456-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፺፫ሚሊዮን ፰መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር /ዘጠና ሦስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Financing Agreement Credit Number 4456-ET signed in Addis Ababa on the 13th day of June 2008 between of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 93,800,000 SDR (ninety three million eight hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of August, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**